# ሃይማኖተ፡ አበው፡ ቀደምት ።

ተጻፈ፡ ከኪዳነ፡ ወልድ፡ ክፍሌ ።

www.ethiopianorthodox.org

ይህ፡ ሃይማኖተ፡ አበው፡ ቀዳምት፡ የተባለ፡ መጽሐፍ፡ ከአለቃ፡ ኪዳነ፡ ወልድ፡ ክፍሌ፡ ተጽፎ፡ ለአቶ፡ ዴስታ፡ ተክለ፡ ወልድ፡ በዐጸራነት፡ ተሰጥቶ፡ ነበር። አሁን፡ በዶክተር፡ ብርሃኑ፡ አበበ፡ አማካይነት፡ ምዕራብ፡ ጀርመን፡ ፍራንክፈርት፡ በሚገኘው፡ በፍሮቤንዩስ፡ ድርጅት፡ እንዲታተም፡ አንዱ፡ ቅጂ፡ ለዶክተር፡ ፕሮፌሰር፡ ኢይከ፡ ሀበርላንድ፡ ተሰጥቷል።

ዐዲስ፡ አበባ፡ ሠኔ፡ ፩፬ ቀን፡ ፲፱፻፷፫ ዓ.ም።

ዴስታ፡ ተክለ፡ ወልድ።

www.ethiopianorthodox.org

መጺና፡ ጣፕም፡ ወይም፡ ዐጭሬ።

በጎች፡ ጠባቂ፡ ይህ፡ መጽሐፍ፡— የቂርሎስ፡ ተረፍ፡
ፍየሎችንም፡ ሲማትር፡— ዐይነብር፡ ዐይነብር።
አይሂችኹ፡ በጎች፡ አትደንግጡ፡— ይህን፡ ሰርዲ፡ ስትግጡ፡
ከዚሁ፡ አለና፡ በመንፈስ፡— እረኞችኹ፡ የሉስ።
ሰርዱውም፡ ታሪክ፡ የሚያጠግብ፡— ለሚግጠው፡ ከልብ፤
አለልብ፡ ጣን፡ መጋፕ፡— የበሬሮ፡ ፈሊፕ፤
ወይም፡ የምሁሮች፡ ትምርት፡— መጣፍ፡ ማበላሸት።
ደንብራችኹም፡ በንባቡ፡— ገደል፡ ትርጓሜ፡ እንዳትገቡ፡
አሌ፡ ወርቅ፡ ነው፡ አሌ፡ ወርቅ፡— አፋፍ፡ የሚጠብቅ።
በኹለት፡ ዐይኑ፡ ባሕርይ፡— ቃል፡ ሥጋ፡ ኮነን፡ እንዳያይ፡
ዐይኑን፡ ጨፍኖ፡ እንደናባ፡— ማነው፡ ገደል፡ የገባ።

የመጻሕፍት፡ ዐዋጅ።

ምስጢረ፡ ሥላሴ፡ ምስጢር፡ የተባለ፡
ምንታዌ፡ ርባዔ፡ በርሱ፡ ስለሌለ፤
ዘርፉም፡ በ፫፡ ሠይል፡ ሥላሴ፡ ሲባል፡
ባንድ፡ መለኮት፡ ባ፫፡ አካል፤
አካሉ፡ እንዴ፡ ብረት፡ ሳይጨፈለቅ፡
መለኮቱ፡ እንደንጨት፡ ሳይሰነጠቅ፡
ዘላለም፡ ሥላሴ፡ ዘላለም፡ ዋሕድ፤
የማያንስ፡ የማይጐድል፡ የማይፈደፍድ።
ከተከፈለማ፡ ባሕርይ፡ እንዴ፡ ርስት፡
ከሦስትነት፡ በቀር፡ የለም፡ አንድነት።
ምስጢረ፡ ሥጋዌም፡ ምስጢር፡ የተባለ፡
ቱሳሔ፡ ቡዓዴ፡ በርሱ፡ ስለሌለ፤
ዘርፋና፡ ቅጽሉም፡ ወልድ፡ ዋሕድ፡ ወበኵር፥
ባለ፪፡ ባሕርይ፡ ባለ፪፡ ግብር፤
ልዑልና፡ ትሑት፡ አምላክና፡ ሰው፡

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

፬

ሰው፡ኹሉ፡እንደ፡ቶማስ፡የሚዳስሰው።
 ምስጢረ፡ቅባቱም፡በአዳም፡ሲለካ፡
እንደ፡ጕዣምም፡ቅባት፡የለውም፡አሙካ፤
በኋላቱ፡ሀብታት፡በጸጋ፡አሬዋት፡
ሒኖክ፡ኢሳይያስ፡ ስላጣሬጡት።
የተቀብዐ፡ስሙም፡አዳም፡ዳግማይ፡
ከዳግሚት፡ሔዋን፡በነሣው፡ባሕርይ፤
ከመልከ፡ጼዴቅም፡በነሣው፡አርአያ፡
ንጉሠና፡ካህን፡ነቢይ፡ሐዋርያ።
 ሃይማኖተ፡አበው፡ረኹሙ፡ሐብሉ፤
እንዲህ፡ባጭር፡ዐዋጅ፡ይጠቀለላል።
በትምርት፡ቻግሮ፡ዐይንን፡ካልገለጡ፡
ወይ፡መምርነት፡ምንም፡ቢያንጋግጡ፡
የተሰብአ፡ዳግት፡የተቀብዐ፡መውጫ፡
አፋፉ፡አይታይም፡በሽፍግ፡ባፍ፡ብልጫ።
 እየተጊደደ፡በልቦለድ፡ባህሉ፡
ወንጌልን፡ለሚሰም፡ለሚሳለም፡ኹሉ፡
ዐዋቆች፡ካልሰጡት፡ማረሚያና፡ዐራሚ፡
ንፍግ፡ይለቀልቃል፡አላዋቂ፡ሳሚ፤
ባልሰላ፡ባልሾለ፡በዱልዱም፡ጫሲና፡
ምስጢረ፡ሠጋዊ፡መቼ፡ይወጋና።
 ምስጢሩን፡ሳያውቁ፡መተርጐም፡መጥቀስ፡
ዳፍሮ፡ሳይበጡ፡ዐማም፡ደም፡እንደ፡ማፍሰስ።
ወይም፡ናላ፡ዞሮ፡በሐሞት፡ብዛት፡
ሳይተፉ፡እንደ፡ማለም፡እንደ፡መቃዠት።
መጣፉን፡ገላልጠው፡ምስጢር፡ለማይቀምሉ፡
እወና፡አልቦ፡ነው፡ነገራቸው፡ኹሉ፤
፩፡ባሕርይ፡እያሉ፡ቱሳሔ፡የለም፤

www.ethiopianorthodox.org

ትሬትፍቷል፡ ብሎ፡ አልተቈረሰም።
በመሳ፡ በጣምት፡ በነሲብ፡ ትርጓሜ፡
ጰመናውን፡ ጠቅሶ፡ ቷፍኖ፡ በጊሜ፡
፩፡ ባሕርዪ፡ ወልድ፡ ቅብ፡ ፫፡ መለኮት፡ ባዪ፡
የ፫ቱ፡ ጉባኤ፡ ተጣዪና፡ አጣዪ፤
ወዪም፡ ፈራሽ፡ አፍራሽ፡ ዘመን፡ አመጣሽ፥
ልቦለድ፡ ፈጠራ፡ የመነኰሴ፡ ጉሽ፤
ከተንቢኖቹ፡ ፕንስስ፡ ከቢዘን፡ ድፍድፍ፡
የተበጠበጠ፡ በቷሳቅ፡ ጋናፍ።
ሳትሞት፡ ሞተች፡ ብለው፡ ምንም፡ ቢቀብሯት፡
አትሞትም፡ አትሞትም፡ አትሞትም፡ እውነት።
እውነት፡ የማዜር፡ ገንዘብ፡ እንደማዜር፡ ባሕርዩ፡
ዘሳለም፡ ሕያው፡ ናት፡ በምድር፡ በሰማዩ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፯

የተዋሕዶ፡ ባሕል፡ ንዋየ፡ ውስጥ፥ ሐተታውን፡ በግኘም፡ የሚገልጥ።
የበሰለው፡ ትምርት፡ እንጀራና፡ ጠጅ፡
ሲበላ፡ ሲጠጣ፡ በትርጓሜ፡ አውራጅ፡
በኵራችን፡ ወልደ፡ አብ፡ ወልደ፡ ማርያም፡
ከሚያድለው፡ ጸጋ፡ ሳይቀምስ፡ አይሰኝም።
ሳይቀምስም፡ ቢሰኝ፡ ያን፡ እሳቱና፡ ዐውሎ፡
ማን፡ ይጠጣው፡ ነበር፡ ዱፍሮ፡ ተቀብሎ።
ያባት፡ የናቱ፡ ርስት፡ መስጠት፡ መቀበል፡
ጸጋ፡ የሚያፈራ፡ ልደት፡ የሚያበቅል፡
በማይታበለው፡ በኪዳኑ፡ ቃል፡
እንደ፡ ራስ፡ ወሌ፡ አገር፡ የጁ፡ ይባላል።
ቀኙ፡ ዘየዐሊ፡ ግራው፡ ተወካሬ፤
ሰጪና፡ ተቀባይ፡ ቀጂና፡ አሳሳሬ፤
የክህነት፡ የመንግሥት፡ ገበሬና፡ ጣሬ፤
ፍጹም፡ ባለጸጋ፡ ለጋስ፡ እጁ፡ ሰሬ።
ግብር፡ ሳያስታጕል፡ አስታጕሏል፡ እያሉ፡
ክርስቱ፡ እንዲደነቅሉት፡ መናፍቃን፡ ኹሉ።
በባሕርዩ፡ ሲሰኝ፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡
እንደ፡ ሰውነቱ፡ ተቀባይ፡ ቢሆን፤
የነቀፈው፡ የለም፡ አንድ፡ ያነወረው፡
ከኪልቄዶን፡ በሬት፡ ከኘቀመ፡ ራግው፡
ቋንቋ፡ ሳይለያይ፡ ሳይበትን፡ ሰው፡
በሦስቱ፡ ጉባዔ፡ ከነበሩ፡ አበው።
ኂሳም፡ ከትነሡት፡ ከሰብእ፡ ምሥራቅ፡
ከናባ፡ ሳዊሮስ፡ ካንጾኪያው፡ ሊቅ፡
እስከናባ፡ ትክሌ፡ የቴሳው፡ ዲቂቅ፡
ሐዲስ፡ ሐዋርያ፡ ሰማዕት፡ ወጻድቅ፤

www.ethiopianorthodox.org

፩፲

የሃይማኖት፡ፍሬ፡ከቤቱ፡እንዲይጠሩ፡
ተክለ፡አሚን፡ብሎ፡የሰየመው፡አሌፉ።
ከከሣቴ፡ብርሃን፡ካንደኛው፡ሰላማ፡
እስካፄ፡ሱስንዮስ፡ዲኖና፡ጨለማ።
የኢትዮጵያ፡ትምርትና፡እምነት፡
ይኸ፡ነው፡ይኸ፡ነው፡ይኸ፡ነው፡ከኘንት፤
ኋላ፡የመጣ፡ነው፡ካራና፡ቅባት፡
በሱስንዮስ፡ዘመን፡በፋሲል፡መንግሥት።
ዕውር፡ዘኢየሱስ፡የቅባቱ፡ቅል፤
የካራውም፡አሮት፡አዛዥ፡ዘድንግል፤
አሽሟጣጩም፡ኪኑ፡በትሩ፡ዐምዴ፡መንሱቱ፤
ሎሚታው፡ወልድ፡ቅብ፡የተሰካበት።
ስለቱ፡ዲንዲሱ፡ሀለሳይ፡ሰላማ፡
የቤተ፡ክሲያን፡ጭጋግ፡የወንጌል፡ጨለማ፡
ወልዋዩ፡ሰንጋዩ፡ከተንቤኖች፡ጋራ፡
ዮሐንስ፡ዘትግሬ፡ቴዎድሮስ፡ዘቋራ።
የቴዎድሮስ፡ይብቃ፡የሚሉት፡ዐዋጅ፡
ስላልተሠረዘ፡በወራሾቹ፡እጅ፡
ምኒልክም፡ታኘቆ፡ባዋጅ፡ሲመዘው፡
ዐማራና፡ትግሬ፡የሚጨብጠው።
ውሳጋው፡ኛንብራው፡መክዱና፡እጅታው፡
መምህር፡አካለ፡ወልድ፡የቦሩ፡ሚዳው።
ተሸፍኖ፡ሲኖር፡ትርጓሜው፡ኀፍረት፡
፫፡መለኮት፡ብለው፡የገላለጡት፤
ከመጣፍ፡ተጣልቶ፡ትርጓሜያቸው፡ከንቱ፡
የሥላሴን፡ባሕርይ፡ስለ፡ፈነከቱ፡
በግዝት፡ሰንሰለት፡በርግማን፡አሸክላ፡
ታስረው፡እስኪፈቱ፡ከሞቱ፡በኋላ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፱

ኦርቶዶክስ፡ማለት፡ርቱዕ፡ባህል፡
የሰብአ፡ኒቅያ፡ስምና፡ቅጽል፡
ተዋሕዶም፡ማለት፡የኢሬሶን፡ስም፡
ፍቺው፡ከኦርቶዶክስ፡ዙሮ፡የሚገኝም።
የዛሬ፡ዘመን፡ልጅ፡አባቱን፡አያውቅ፥
በቄርሎስ፡ፈንታ፡አውጣኪን፡ናፈቅ፡
ተዋሕዶ፡ሳይሆን፡ስሙ፡ሃይማኖቱ፡
ኦርቶዶክስም፡ሳይኖን፡ባህሉና፡ትምርቱ፡
ሰርቅና፡ቀምቶ፡የሰው፡ስም፡በከንቱ፡
ሰው፡ሁሉ፡አለስሙ፡ምነው፡መጠራቱ።
የተዋሕዶ፡ባህል፡የኦርቶዶክስ፡ዜማ፡
፩፡ባሕርይ፡ወልድ፡ቅብ፡ማለት፡ከሆነማ፡
በሰሜው፡ቋንቋችን፡በግእዝ፡ከተማ፡
ኅብሩይ፡ሐዲስ፡ሊቃውንት፡የሉማ።
ትርጓሜ፡ፈታዮች፡አፍጣኙና፡አቅጣኙ፡
ከመዳሮው፡ንባብ፡እስከትገናኙ፡
ባላው፡ከደንቆሮው፡እንዲለይሏችኹ፡
ኸማኔ፡መጠየቅ፡አያሳፍራችኹ፤
ኸማኔውም፡ግዕዝ፡ንባብ፡ቋጣሪው፡
የማይበጣጠስ፡ትርጓሜ፡ዝሓው።
ይህን፡ተሰጦ፡የማይቀበል፡
የማርቆስ፡ልጅ፡ነኝ፡ብሎ፡ቢያፈችል፤
ወይም፡እኔን፡ስሙኝ፡በወልድ፡ቅብ፡ዜማ፡
እያለ፡ቢወገሽ፡እንዳባ፡ሰላማ፡
የብሉዩን፡ሎሬ፡የሐዲሱን፡ቁምጣ፡
ሊቅ፡እንደ፡መኾኑ፡ባጭር፡ታጥቆ፡ይምጣ፡
ዘመን፡የወለደው፡ከሰይጣን፡አርግዞ፡
ንጉሡ፡በወደደው፡ሰይፉን፡ተመርኵዞ፡

www.ethiopianorthodox.org

፴

በሰላማ፡ዱለት፡ እንደ፡በግ፡ሸንፍላ፡
የሰው፡ራስ፡ምላስ፡ተቈርጦ፡እስኪበላ፡
የቴዎዶሮስና፡የዮሐንስ፡ይብቃ፡
በተባለው፡ዐዋጅ፡በምኒልክ፡ሳንቃ፡
ስለ፡ተዘጋበት፡የተማሬ፡ቤቱ፡
ተዳፍኖ፡ይኖራል፡ኦርቶዶክስ፡እሳቱ፡
የጠፋ፡ይመስላል፡እሳት፡ቢዳፈን፤
ገላልጦ፡እስኪያነደው፡ጊዜና፡ዘመን።
ተርብም፡ዝንብ፡ይመስላል፡የማይናደፍ፡
እስኪቈሰቍሱት፡በሌባ፡ጣት፡ጫፍ፤
ሲቈሰቍሱት፡ግን፡ቈስቋሹን፡ሰው፡ነድፎ፡
ማሀናቱ፡አይቀርም፡እሮ፡እንጋ፡እሮ።

በመዠመሪያው፡ክፍል፡ምክንያተ፡ጽሒፍ፡ሲጨረስ፥የመጻሕፍት፡ዐዋጅ፡ተብሎ፡የተጣፈውን፡ዐጭሬና፡ረዥም፡ግጥም፡ተመልከት፤ ከዚህ፡ጋራ፡አንድ፡ነው።

## ክፍል፡ካልእ፡
## በእንተ፡ቅብዐት።

የቅባቶች፡ባህል፥ ሠለስቱ፡ዕድዋኒሁ፡ለሰብእ፡እንዲ፡ተባሉት፡(ዓለም፡ሥጋ፡ሰይጣን) ፫፡ወገን፡ነው። መዠመሪያ፤ በፋሲል፡ዘመን፡የተነሡት፡እነዘኢየሱስ፤ መጽሐፍ፡እንደየ፡ርእሶ፡ እንዘ፡ባዕል፡ይላልና፤ቃል፡በተዋሕዶ፡ዜግ፤ ዜጋ፡ኾነ፤ ከሥጋ፡ሲዋሐድ፡የባሕርይ፡ክብሩን፡የባሕርይ፡ልጁቱን፡ዐጣ፡ለቀቀ፤ ሲቀባ፡ግን፡ወደ፡ጥንተ፡ክብሩ፡ተመልሶ፡በሰውነቱም፡ባምላክነቱም፡፩ ወገን፡በቅባት፡የባሕርይ፡ልጅ፡ኾነ፡ብለዋል። ፪ኛ፡ባንደኛው፡ዮሐንስ፡የተነሡ፡እናካለ፡ክርስቶስ፤ዜግ፡ማለትን፡ነቀፈው፡አጸይፈው፤ መጽሐፍ፡እስመ፡ተዋሕዶ፡አእተታ፡አምንታዊ፡ይላልና፤ ሥጋ፡በተዋሕዶ፡፩፡አካል፡ሆነ፡እንጂ፤ የአምላክነት፡ክብር፡አላገኘም፤ሲቀባ፡ግን፡ክብር፡ተላለፎለት፥ተፈኘሮ፡ተገብሮ፡ጠፍቶለት፡በቅባት፡የባሕርይ፡ልጅ፡የባሕርይ፡አምላክ፡ኾነ፡ብለዋል። ፫ኛ፡በቴዎዶሮስ፡

www.ethiopianorthodox.org

እንደ፡ፌርያን፡ልቧን፡አክብዶ፡አስተባብላታለች፤የኢትዮጵያም፡ሰዎች፡በሥራቸው፡ኹሉ፡እንደ፡እስራኤል፡ስለ፡ኾኑ፥የኒቅያ፡ሕግ፡ነፃ፡ካወጣቸው፡በኋላ፡ወደ፡ባርነት፡በመመለሳቸው፡እግዚርን፡አሳዝነውታል።የኒቅያም፡ግዝትና፡ርግማን፡እንደ፡ካህኑ፡እንደ፡ሤንሐስ፡ዘገር፡ኢትዮጵያን፡ሳይለዩና፡ሳይስት፡ከግብጽ፡ጋራ፡አጣምሮ፡፪ቱንም፡ዘለቄ፡አወጋግ፡ወግቷቸዋል።ለነሱ፡ግን፡አልተሰማቸውም፤አፍዝ፡አደንግዝ፡ተቀብተዋልና፡(ዘኍ፳፭፡፰)።ፍትሐ፡ነገሥት፡አንቀጽ፡ራብዕ፤ዘኒቅያ፡፴፡ወ፳፪።

ሠለስቱ፡ምእት፥ሊቃነ፡ጳጳሳት፡በዚህ፡ዓለም፡እንዲራቱ፡ኪሩቤልና፡ወንጌላውያን፥እንዲራቱ፡አፍላጋትና፡ወንጌላት፥እንዲራቱ፡ማዕዝንና፡ክፍለ፡ዘመን፥እንዲራቱ፡ነፋሳትና፡ጠባይዐ፡ፍጥረት፡፬ብቻ፡ይኹኑ፡ብለው፤ልቅናውን፡ለሮምያና፡ለእስክንድርያ፡ለኤፌሶንና፡ለአንጾኪያ፥ለነዚህ፡ኣራቱ፡ከሰጡና፡ካደሉ፡በኋላ፤ለሠልቅና፡ለኢትዮጵያም፡ለኹለቱ፡ታላላቅ፡አገሮች፡ከነዚህ፡ከአራቱ፡የሚያንስ፡ከሌሎች፡አህጉር፡የሚበልጥ፡መካከለኛ፡ሕግና፡ማዕርግ፡አቁመዋል።የሠልቁን፡ማዕርግ፥ወራብዕ፡በዓለ፡መንበረ፡አንጾኪያ፥ወውእቱ፡መንበረ፡ጴጥሮስ፡ካዕበ፥ካለው፡አያይዘው፤ዘ፴ወ፰።ወያክብርዎ፡ካዕበ፡ለበዓለ፡መንበረ፡በግዳድ፥ዘውእቱ፡ሠልቅ፡እንተ፡ውስተ፡ብሔረ፡ምሥራቅ፥ወዲእቲ፡ሀገረ፡ምድያም።ወያዕብዩ፡ለዝንቱ፡ካዕበ፡በስመ፡ሊቃናት።ወያብሕዎ፡ለቱኒ፡አምዲእዜ፡ከመ፡ያጽድሶ፡ጳጳሳተ፡በከመ፡ይገብሩ፡ሊቃነ፡ጳጳሳት፤ከመ፡ኢይጻምዉ፡ምሥራቃውያን፡በሐዊሮቶሙ፡ኀበ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡አንጾኪያ፥አው፡በተመይጦቶሙ፡እምኀቤሁ።እስመ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡አንጾኪያ፡ነዋ፡ሠምረ፡በዝንቱ፡እምድኅረ፡ሰአልዎ፡ለቱ፡ጉባኤ፡ማኅበር፡ከመ፡ኢይሕዝን፡በእንተ፡ዘተአተተ፡እምኔሁ፡ለሥልጣነ፡ምሥራቅ፤እስመ፡ውእቱ፡ኢኀሠሠ፡ዘንተ፡ግብረ፡ዘእንበለ፡ከመ፡ያብእሙ፡ውስተ፡ዕረፍት፡ለክርስቲያን፡ዘብሔረ፡ፋርስ።ዘ፴፡ወ፱።ወለእመ፡መጽአ፡ግብር፡ዘይትጋብኡ፡ቦቱ፡ኤጲስ፡ቆጶሳት፡ውስተ፡ብሔረ፡ሮም፥ወመጽአ፡ኀቤሆሙ፡በዓለ፡ዛቲ፡ሢመት፡ዘውእቱ፡በዓለ፡ሠልቅ፤እንተ፡ይእቲ፡እምርት፡ሀገረ፡

www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያኑ፡ በአንጾኪያ፡ ቀዲሙ፡
(ኢሳ፡ ፯፬፡ ፬ ። ግብ ፲፮፡ ፳፫)።

መዲና፡ ግኙም፡ የአዕማድ፡ መቅድም ።

የሰማይና፡ የምድር፡ — አባት፡ እናት፡ እግዚር፡
እሊህን፡ መንቶች፡ እሑድ፡ — ፩ጊዜ፡ ፀንሶ፡ ሲወልድ፡
ሳያስጨንቀው፡ መፍጠር፡ ምጡ፡ — ወዲያው፡ በቅጽበት፡ ወጡ ።
አዋላጆቹም፡ ኹለት፡ — ክሂልና፡ ሥምረት፡
በመንፈሱና፡ በቃሉ፡ — ማሪያም፡ ማሪያም፡ የሚሉ ።
ያራስ፡ ጥሪውም፡ ምስጋና፡ — ቀረበለት፡ በጕህና፤
ካህናቱ፡ ሰማይ፡ ሱራፌል፡ — በቅዳሴ፡ ጠበል፡
ቤቱን፡ አካሉን፡ እየረጩ፡ — እንደ፡ ወንሮች፡ ሲንሚጩ፡
ሳኞ፡ ጠፈርን፡ ሲያሰናዱ፡ — ምድር፡ ቤቱንም፡ ላርብ፡ እንግዳ፡
ማክሰኞ፡ ደግሞ፡ በዩብስ፡ — ብዙ፡ ዐይነት፡ ድግስ፡ ሲደግስ፡
አገልጋዩና፡ ረዳቱ፡ — ደኹን፡ ደኹን፡ ባደቱ፡
ጥበቡ፡ ብቻ፡ ነበረች፡ — በመንፈሱ፡ ያለች ።
የምድር፡ ዐዋቆች፡ ሳይበቅሉ፡ — ሳብአ፡ ሰገልም፡ ሳይባሉ፡
የሰማይ፡ ኰከብ፡ ቈጣሪ፡ — ማነው፡ አለፈጣሪ ።
ዐውዱ፡ ነገሠቱስ፡ ፀሓይ፡ — ከጨረቃ፡ በላይ፡
የተዘረጋው፡ ሮብ፡ — ቀን፡ ቀን፡ እንዲነበብ ።
በናጌብ፡ ውሃ፡ በሲሶው፡ — ሳኞ፡ በተቀዳው ።
ያኑኑ፡ ደግሞ፡ ሮብ፡ ለት፡ — ፀሓይ፡ አሙቀለት፡
ሲያስታውክና፡ ሲያስመልስ፡ — ሮብ፡ ማታ፡ ላሙስ፡
የወጣው፡ ፍጥረት፡ ከባር፡ ሆዱ፡ — አይታወቅም፡ ፍቅዱ፤
የንግዱ፡ ልጅም፡ ዲያብሎ፡ — ወረደለት፡ በጕሎ ።
ሰማይና፡ ምድር፡ እንክብል፡ — የሠላሴ፡ ዕንቍላል፥
ያለም፡ ስሙ፡ ግን፡ ሰፋሬ፡ — የመጽሐፉም፡ ኁላሬ፥
ይህን፡ ዕንቍላል፡ በጁ፡ ይዞ፡ — እንደ፡ ጥና፡ ወዝውዞ፡
ማነው፡ አፍርጦ፡ ያሳየን፡ — አለብሉይ፡ ኪዳን ።

www.ethiopianorthodox.org

፸፬

በሲና፡ያዩዋት፡ሔኖክ፡ሙሴ፡— ቅድስቲቱ፡ሥላሴ፡
ያልዘራችውን፡የምትበላ፡— የአብርሃም፡ሸመላ፤
ቅኔ፡ማሕሌትም፡ሲሏት፡— ቤቷ፡ስድስት፡ዕለት፥
ቅድስትም፡ሲሏት፡በተሥላሷ፡— ቅዳሜ፡ነው፡መቅደሷ።
እንዳይገማባት፡በኅቡብ፡— የንቊላሏ፡ከበብ፡
ከእሑድ፡እስከ፡ዐርብ፡ታቅፋ፡— አያሞቀች፡በተሰፋ፡
ስትፈለፍለው፡እንዳሸት፡— ያነን፡ኹሉ፡ጫጩት፡
እናትነቷ፡እንደ፡ዶሮ፡— አያትነትን፡ጨምሮ፡
ልጅ፡የልጅ፡ልጇን፡ሲጐበኝ፡— ሎኛን፡መስሎ፡ታየኝ።
ኻያ፡ኹለቱን፡ነገድ፡— ከሑድ፡እስከ፡ዐርብ፡ስትወልድ፡
የነገድ፡ኹሉ፡መጨረሻ፡— አዳም፡የባብ፡መዶሻ፤
ወይም፡ብንያም፡ወልደ፡ጻዕር፡— የተፋችው፡ምድር፤
ከኋቱም፡ሥጋው፡መሬት፡— ዘር፡ካሎዳቀበት፡
በዳግመኛው፡ዐርብ፡እስክትበቅል፡— ሔዋን፡የገቦ፡እኽል።
አዝመራው፡ፍጥረት፡በሔዋን፡— ከተከተተልን፡
ሥላሴን፡ይዘን፡እንብረር፡— ወዴ፡ጥምቀተ፡ባሕር።
ያለቃ፡ዕንቍ፡ባሕርይ፡ግጥም፡ስለ፡ሥነ፡ፍጥረት፡ከፍልና፡ስም።

፬ቱ፡ባሕርያት፡፯ቱ፡ሰማያት፡
ሕያዋን፡መላእክት፡ብርሃንና፡ጽልመት፡
እነዚህ፡ስምንቱ፡ተፈጥረዋል፡እሑድ፡
በረቂቁ፡ባሕርይ፡በሥላሴ፡ፈቃድ።
ውሃን፡ከ፫ ከፍለው፡አንዱን፡እጅ፡አጽንተው፡
በነፋስ፡ተራዳ፡ወደ፡ላይ፡ዘርግተው፡
በዕለተ፡ሠኑይ፡ፈጠሩ፡ሥላሴ፡
ኤሎሂም፡አዶናይ፡አጋዕዝተ፡ሙሴ።
አዝርዕቱም፡አትክልቱም፡ከዕፀዋት፡ጋራ፡
ማግሰኞ፡ተገኙ፡በመለኮት፡ሥራ።
ፀሓይን፡ጨረቃን፡ኮከብን፡ጨምሮ፡

www.ethiopianorthodox.org

ረቡዕ ፡ ፈጠረ ፡ በቃሉ ፡ ተናግሮ ።
ጓሙስ ፡ ከባሕር ፡ ውስጥ ፡ የፈጠራቸው ፡
እንስሳት ፡ አራዊት ፡ አዕዋፍ ፡ ናቸው ፡
የኀሙስን ፡ ፍጥረት ፡ በመልክ ፡ የሚመስሉ ፡
ዐርብም ፡ ከየብስ ፡ ላይ ፡ ፈጠረ ፡ በቃሉ ።
ደግሞ ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፡ በ፫ኛው ፡ ሰዓት ፡
አዳምን ፡ ፈጠረ ፡ ሊያኖረው ፡ በገነት ።
ቀዳሚት ፡ ዐረፈ ፡ ሥራውን ፡ ቢጨርስ ፡
ድካም ፡ የሌለበት ፡ የዘላለም ፡ ንጉሥ ።
ፈጥሮ ፡ ለሚገዛን ፡ ለሚመግበን ፡
ክብርና ፡ ምስጋና ፡ ኀይልና ፡ ሥልጣን ፤
ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ፡ ወአሜን ።

አዕማደ ፡ ምስጢር ፡ ምስለ ፡ አዝፋሪሆን ፡ ወጸዋትዊሆን ፤ ዘበተርጓሚሁ ፡ ትምህርተ ፡ ክርስቲያን ፥ በበ ፡ ጸታሁ ፡ ወበበ ፡ መትለሙሁ ፤ ዘውጹእ ፡ ወእስትጉቡእ ፡ እምከርሠ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ እምላካውያት ፥ ወእምአፈ ፡ አበው ፡ ሊቃውንት ፡ ጽኑያነ ፡ ምግባር ፡ ወሃይማኖት ። እኮስ ፡ ፀአቶሙ ፡ ወተጋብኦቶሙ ፡ በነዋኀ ፡ ቃል ፤ አላ ፡ ኀጹረ ፡ ወኀዲጠ ፡ በዘየአክል ፥ ለአንባቢ ፡ ወለሰማዒ ፡ ምእመን ፡ ንቁሀ ፡ ልብ ፡ ወጽሉወ ፡ እዝን ።

አንቀጽ ፡ ቀዳማዊ ፡ በእንተ ፡ ምስጢረ ፡ ሥላሴ ።

መጀመሪያ ፡ ክፍል ።

ጥያቄ ፤ እውነተኛ ፡ መምህር ። ምን ፡ ሰው ፡ ነህ ።

ምላሽ ፤ ዐዋቂና ፡ ብልኅ ፡ ዲቀ ፡ መዝሙር ። በግዜር ፡ አጋዥነት ፡ ክርስቲያን ፡ ነኝ ።

ጥያቄ ፤ በምን ፡ ታምናለህ ።

ምላሽ ፤ በግዜር ።

ጥያቄ ፤ እግዜር ፡ ስንት ፡ ነው ።

ምላሽ ፤ አንድም ፡ ነው ፤ ሦስትም ፡ ነው ።

ጥያቄ ፤ አንድነቱ ፡ በምን ፡ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ነውና፤ ፫ቱን፡ አካላት፡የሚያስገኝና፡የሚያዋሕድ፡ስለ፡ኾነ፡ ነው።

ጥያቄ፤ ባስገኝነቱስ፡ባሕርይ፡ከአካል፡ይቀድማልን።

መልስ፤ ባነጋገር፡እንጂ፥ በመኖር፡አይቀድምም፤ ምንም፡አስገኝና፡ መገኛ፡ቢኾን፡መቅደምና፡መከፈል፡የለውም። ባነጋገር፡ግን፡ የቍጥር፡መሠረት፡፩፡ስለ፡ኾነ፥ ከሕንጻ፡መሠረት፡እንዲ ቀድም፥ ከ፫ት፡፩ነት፡ይቀድማል፤ ነገር፡ከሥሩ፡ውሃ፡ከ ጥሩ፡እንዲሉ።

ጥያቄ፤ የባሕርይ፡ዘይቤ፥ ምሳሌው፡ትርጓሜው፥ እንዲህ፡ባስገኝ ነት፡ከቆመ፥ ያ፩ነትና፡የ፫ነት፡ምስጢር፡ሐተታው፡እንዴት፡ ነው።

መልስ፤ ላንድ፡በቀል፡ዛፍ፡ ፫ ዐጽቅ፡ቢኖረው፥ የዐጽቅና፡የመትረብ፡ ፫ነት፡ጕንዱንና፡ነቁን፡ ፫ እንዳያሠኝ፤ ባሕርይም፡ባለ፫፡አ ካል፡ስለ፡ኾነ፡በአሐዱነቱ፡አካላትን፡አሐዱ፡አምላክ፡ቢያ ሰኝ፡እንጂ፤ አካላት፡በሦስትነታቸው፡ርሱን፡አንዱን፡፫፡ ሊያሠኙት፡ከ፫ ሊካፈሉት፡አይቻልም። የጕንድና፡የነቅ፡ ፩ነት፥ ፫ቱን፡ዐጽቆችና፡፫ቱን፡መትረቦች፡፩፡ዛፍ፡፩፡ም ንጭ፡አሠኙ፡እንጂ፤ ፩፡ዐጽቅ፡፩፡መትረብ፡እንዳሳሠኙ፥ ባሕ ርይም፡ከርሱ፡በሚነሡት፡በባሕርይ፡ስማቸው፡አሐዱ፡ አምላክ፡አሠኛቸው፡እንጂ፤ አሐዱ፡አካል፡አሳሠኘምና፤ የአካላት፡ቅጽል፡ሠለስቱ፡ለባሕርይ፡አይኾንም፤ አለዚያ፡ ግን፡፫፡አምላክ፡ያሠኛል።

ጥያቄ፤ ለዚህስ፡ምን፡ምስክር፡አለው።

መልስ፤ ብሉይና፡ሐዲስ፡ሊቅ፤ ከሊቃውንት፡አንዱ፡አግናጥዮስ፡ እጕዛን፡በፅምረቱ፡አሐዱ ፡ መለኮት፤ ዘውእቱ፡አሐዱ፡ ብርሃን፡ዘይሠርቅ፡እምኔሁ፡ለሥላሴ፡እንዳለ። ሬጥሮ፡መግ ዛት፥ መፍጠር፡ማስገኘት፡የባሕርይ፡ግብራቸው፡ስለ፡ኾነ፥ ባሕርያን፡በሥርና፡በነቅ፡መስሎ፡አሐዱ፡መለኮት፡ካለው፡

www.ethiopianorthodox.org

ነውና፤ እንደነዚህ፡መቀላቀልና፡መከላከል፡ሳይኖር፡፫ነት፡
ሳይጠሉ፥፫ቱ፡ኹሉ፡ባ፩ነት፡በምልአት፡ይኖራሉ። ባ፩ነት፡
መኖር፡እንደ፡ባሕርያቸው፡አካላቸውን፡አያዋሕደውም፤
ነፋስና፡ብርሃን፡ሙቀት፡ተዋሕደ፡እንደሌላቸው። ሠለስቱ፡
ህላዌ፡በአካላት፤ ወአሐዱ፡ህላዌ፡በመለኮት፡እንዳለ፡(ባስል፡
ዘቂሳ፡ሃይ፡አበ)። ያካል፡ህልውና፡ኺሳ፡በቦታው፡ይመጣል፡
ያልነው፡ይህ፡ነው።

ጥያቄ፤ በአካል፡ስምና፡በአካል፡ግብር፡፫፡መባላቸው፡እንደ፡ምን፡ነው።

መልስ፤ መዠመሪያው፡አካል፡አብ፡ይባላል፤ ፪ኛው፡አካል፡ወልድ፡ይባ
ላል፤ ፫ኛው፡አካል፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ይባላል። ይህም፡ስም፡
አካል፡በተለየ፡ሥራው፡የሚጠራበት፥ ከአካልና፡ከግብር፡የ
ወጣ፡የግብር፡ስም፡ነው። ግብር፡ማለትም፡ሥራ፡ማለት፡ነው።

ጥያቄ፤ አወጣጡስ፡እንደ፡ምን፡ነው።

መልስ፤ መዠመሪያው፡አካል፡ግብሩ፡መውለድና፡ማሥረጽ፡ስለ፡ኾነ፤
ቢወልድ፡አብ፡ተባለ፤ ፪ኛው፡አካል፡ግብሩ፡ልደት፡ስለ፡ኾነ፥
ቢወለድ፡ወልድ፡ተባለ፤ ፫ኛው፡አካል፡ግብሩ፡ሠርጸት፡ስለ፡
ኾነ፥ ቢሠርጽ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ተባለ። ወአስማቲሆሙኒ፡ለአ
ካላት፡አኮ፡ግብር፡ከንቱ፥ ሶበ፡ንሰምዮ፡ለአብ፡አበ፥ በእንተ፡
ዘኮነ፡ወላዴ፤ ወለወልድኒ፡ወልደ፥ በእንተ፡ዘተወልደ፡እምአብ፡
ወለመንፈስ፡ቅዱስኒ፡መንፈስ፡ቅዱስ፥ በእንተ፡ዘወጽአ፡እም
አብ፡እንዳለ፡(ሃይ፡አበ)። ይህም፡ስም፡አይፋለስም፤ የአብ፡ስ
ም፡ለወልድና፡ለመንፈስ፡ቅዱስ፡አይኾንም፤ የወልድ፡ስም፡ለአ
ብና፡ለመንፈስ፡ቅዱስ፡አይኾንም፤ የመንፈስ፡ቅዱስ፡ስም፡ለአ
ብና፡ለወልድ፡አይኾንም፤ ስም፡ቢፋለስ፡ምስጢረ፡ሥላሴ፡ይበ
ላሻል። ወእንዘ፡አሐዱ፡ህላዌ፡መለኮት፡አስማትሰ፡ኢየኅብሩ፡
በበይናቲሆሙ። ኢይፈልስ፡ስመ፡አብ፡ለካዊነ፡ስመ፡ወልድ፡
ወመንፈስ፡ቅዱስ፤ ወስመ፡ወልድኒ፡ለካዊነ፡ስመ፡አብ፡ወመ
ንፈስ፡ቅዱስ፤ ወስመ፡መንፈስ፡ቅዱስኒ፡ለካዊነ፡ስመ፡አብ፡

www.ethiopianorthodox.org

ዳግመኛም፡ባሕርያቸውና፡ሕይወታቸው፡፩፡እንደ፡ኹኑ፥ቅድ
ምናቸውና፡ዕሪናቸውም፡፩፡ነው፤ መቅደምም፡መቀዳደም፥
መብለጥ፡መበላለጥ፡የሌላቸውም። አባት፡ከልጆቹ፡እንዲቀድም፡
እንዲበልጥ፥አብ፡ከወልድና፡ከመንፈስ፡ቅዱስ፡አይቀድምም፡
አይበልጥም፤ ይህን፡ኹሉ፡ሥራ፡የባሕርይ፡፩ነት፡ይከለክላል።
ኢይቀድም፡አሐዱ፡እምካልኡ፡ወካልኡ፡እምሣልሱ። አሐቲ፡
ቅድምናሆሙ፡ለሠላሴ። ኢሀሎ፡አብ፡ዘመነ፡ዘእንበለ፡ወል
ዱ፡ወመንፈሱ፡አሐተ፡ሰዓተ፥ወኢከመ፡ቅጽበተ፡ዐይን።
ሠላሴ፡ዕሪት፡ዘእንበለ፡ፍልጠት፡እንዳለ፡(ሃይ፡አበ። ተረ፡ቁር)።

ጥያቄ፤ ልደት፡ሠርጸት፡በምን፡ይለያሉ፤ የኹለቱስ፡ምስጢር፡ፀአት፡
አይደለምን።

ምላሽ፤ ልደት፡ወልድ፡ወፀአት፡መንፈስ፡ቅዱስ፡እምአብ፡ይትነከር፡
ወኢይትነገር። ወፃእኩ፡እምኀበ፡አብ፡ወመጻእኩ። መንፈስ፡
ጽድቅ፡ዘይወፅእ፡እምአብ፡ይላልና፤ ምስጢራቸው፡ፀአት፡
መኾኑ፡እርግጥ፡ነው፤ አይጠረጠርም። ግሳቸውና፡አወጣጣ
ቸው፡ግን፡እንደ፡ስማቸው፡ልዩ፡ነው። ቃልና፡እስትንፋስ፡ከመ
ዝገባቸው፡ከልብ፡ሲወጡ፥ፀአተ፡ቃል፡አፍ፡ያስከፍታል። እስ
ትንፋስ፡ግን፡አያስከፍትም፤ ቃል፡ከልብ፡ወደ፡አፍ፡ሲወጣ፡
ተወለደ፡እንደ፡መባል፡ኹሉ፡ተነገረ፡ይባላል፡እንጂ፤ ተተነፈሰ፡
አይባልም። እስትንፋስም፡ከልብ፡ወደ፡አፍ፡ሲወጣ፡ሠረጸ፡እንደ፡
መባል፥ተተነፈሰ፡ይባላል፡እንጂ፤ ተነገረ፡ወይም፡ተወለደ፡አይ
ባልም። አብን፡ልብ፡አድርገን፡በልብ፡መሰለን፡የቃልና፡የእስት
ንፋስ፡መዝገብ፡ካልነው፡ዘንድ፡ወልድም፡በቃልነቱ፥ከዚህ፡
ምሳሌ፡የተነሣ፡ቃለ፡አብ፡ወቃለ፡መንፈስ፡ቅዱስ፡ተብሎ፡፪
ቱን፡ያገናዝባል፤ ወፅአ፡ተወልደ፥ወልድ፡ተወላዲ፡ሲባል፡
ግን፡ከአብ፡ብቻ፡ነው። መንፈስ፡ቅዱስም፡በእስትንፋስነቱ፡
መንፈሰ፡አብ፡ወወልድ፡ተብሎ፡፪ቱን፡ያገናዝባል፡(አቡሊ
ዘሮም)። ወፅአ፡ሠረጸ፡ሠራጺ፡ሲባል፡ግን፡ከአብ፡ብቻ፡ነው።

www.ethiopianorthodox.org

ቃሉ፡አለመለወጡ፡በ፫ቱ፡አካላት፡ያለ፡መለኮት፡፩፡መኾኑን፡ያስረዳል። እንደዚሁ፡ደግሞ፡፫ቱ፡ኹሉ፡ሕያው፡ሕያው፡ሕያው፤ ሕይወት፡ሕይወት፡ሕይወት፡ይባላሉ፤ ፫ሕያዋን፡፫፡ሕይወታት፡አይደሉም፤ ፩፡ሕያው፡፩፡ሕይወት፡እንጂ፤ ስለ፡ምን፡ቢሉ፥ሕያዋን፡ሕይወት፡መባላቸው፡ባ፩፡መለኮት፡ነውና። ከመ፡ሕይወት፡ወሕይወት፡ቢል፡ግን፥ይህ፡የባሕርይ፡ሕይወት፡አይደለም፤ እንደ፡ልብ፡እንደ፡ቃል፡እንደ፡እስትንፋስ፡ማለት፡ነው።

## ፳ኛ፡ክፍል።

ጥያቄ፤ ህላዌ፡እንደ፡መለኮት፡ባሕርይና፡አካል፡ስም፡ሲኾን፡እንዴት፡ነው።

ምላሽ፤ ህላዌ፡ማለት፡ዘይቤው፥መኖር፡አኗኗር፡ኑሮ፤ ወይም፡ክዋኔ፥መኾን፡አኳኾን፡ኹኔታ፡ማለት፡ነው። ህለወ፡ኮነ፡ቢዕብራይስጥ፡ስንኳን፡ምስጢሩ፡አንቀጹ፡፩፡ነው፤ ህላዌ፡ግን፡በዐረብ፡ጠቢዕ፥በዕብራይስጥ፡ጤባዕ፡ጉፍ፡ይባላል፤ ጠባይዕ፡ማለት፡ነው፤ ባሕርይና፡አካልን፡ያሳያል፤ ይኸውም፡ሊታወቅ፥ግእዙ፡ህላዌ፡ህላውያት፡የሚለውን፡ኹሉ፥የዐረቡ፡ሃይማኖት፡አበው፥ጠቢዓ፡ጠቢዕቴን፡ይለዋል። ህላዌ፡ለቅድስት፡ሥላሴ፥ባሕርይ፡ሲኾን፡አሐዱ፤ አካል፡ሲኾን፡ሠለስቱ፡ይባላል። ሠለስቱ፡አካል፤ወአሐዱ፡ህላዌ። ወለእመ፡ንቤ፡ከመ፡ቃል፡ተወክፈ፡ሕማመ፡በሥጋ፥ንሕነሰ፡ነአምን፡ከመ፡አሐዱ፡ህላዌ፡ዘእምሥላሴ፡ቅድስት፡ተሰቅለ፤ ወካልኣንሰ፡ህላውያት፡ዘቅድስት፡ሥላሴ፡ኢሐመሙ። እግዚአብሔር፡በዓለ፡ሠለስቱ፡ህላዌ፤ አሐዱ፡በባሕርይሁ፡ወሥልጣኑ፡ወመለኮቱ፡እንዳሉ፡(ቅዱ። ሃይ፡አበ። አክሲ፡)። ለሥጋዊ፡ግን፡ህላዌ፡በአንቀጸ፡ተዋሕዶ፡አካል፡ስለ፡ኾነ፤ አሐዱ፡እንጂ፡ክልኤቱ፡አይባልም፤ በአንቀጸ፡ተዓቅቦም፡ባሕርይ፡ስለ፡ኾነ፥ክልኤቱ፡እንጂ፡አሐዱ፡አይባልም። እስመ፡አበዊነ፡ሰመይዎ፡በዝንቱ፡ገጸ፡መካን፡ለህላውያት፡አካላተ፤ አትናቴዎስኒ፡ረሰየ፡ህላዌ፡አሐደ፡አካለ፡ዘእግዚአብሔር፡ቃል፡ዘተሠገወ። ወኢተወለጠ፡ህላዌ፡

www.ethiopianorthodox.org

፺፰

ኹሉ፡ እስከ፡፫፡ሰዓት፡ሬጽሞ፡ይዘጋል። በ፩፡ዕለት፡፫፡ተውሳክ፡
፫፡ሕጸጽ፡አላት። ለጨረቃም፡ይደርሳታል፡ያልነው፡፻፳ ቱ፡ክፍ
ል፡፲፫፡ሎባዌ፡ይኾናል። ይኸውም፡ከዕለት፡ሠርቅ፡እስከ፡ዕለት፡
ግሣሀ፡በየለቱ፡፫፡፫ቱ፡ክፍል፡ወይም፡፫፡፫ቱ፡እጅ፡ይሰጣታል፤
ዳግሞ፡ካ፲፫፡ቀን፡በኋላ፡በየለቱ፡፫፡፫እጅ፡ይነሣታል። እንዲህ፡
ማለት፥የምዕዛሯን፡መከሬት፡መዘጋት፥የ፳ነቱን፡መናገር፡
ነው፡ እንጂ፡በየወሩ፡የሚሰጣትና፡የሚነሣት፡ሌላ፡ብርሃን፡አለ፡
ማለት፡አይደለም። ለፀሓይ፡ምዕዛር፡እንዳላት፥ለጨረቃም፡
ምዕዛር፡አላት፡ብለው፥የቍጥር፡መምህራን፡መጠኑ፡ንጠቱን፡
እንዲህ፡አምልተው፡አስፍተው፥ወሰን፡ድንበር፡ሰጥተው፡ይሬ
ቱታል።

ጥያቄ፤ ከመለኮትና፡ከህላዌ፡ከብርሃንም፡ሌላ፥ ብዙ ፡ ምሳሌና፡
የምሳሌ፡ስም፡እንዳላቸው፡ነግረኸኛልና፤ የምሳሌውን፡ስ
ሙን፡ጠርተኸ፡ሩሱን፡ቍርተኸ፡ኣሳየኝ።

ምላሽ፤ ሊቁ፡አባ፡ሕርያቆስ፡ሥላሴን፡በፀሓይ፡በእሳት፡በኅሐ፡በዥንደ፡
ወይን፡መስሎ፡ካሳየ፡በኋላ፤ ቅዱስ፡ጲጥሮስ፥ወአፍቅሩ፡ሐሊበ፡
ነባቤ፡ዘአልቦቱ፡ቱስሕት፡ከመ፡ቦቱ፡ትልሐቁ፡ለድኂን፡ያለ
ውን፥ ቅዱስ፡ጳውሎስም፥ ወትፈቅዱ፡ሐሊበ፡ይውግዑከሙ፤
ወአኮ፡መብልዐ፡ጽጕዕ፡ጽኑዐ፤ እስመ፡ኵሉ፡ዘይትወጋዕ፡ሐሊ
በ፡ሕፃን፡ውእቱ፡ያለውን፡መሠረት፡አድርጎ፥ አብ፡ሐሊብ፤
ወልድ፡ሐሊብ፤ ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ሐሊብ፤ አሐዱ፡ ውእቱ፡
ሐሊብ፡ ዘአልቦቱ፡ቱስሕት፡ ብሎ፡ምሳሌና፡ስም፡ሰጥቷል።
ትርጓሜውም፡ይህ፡ነው፤ የሐሊብ፡መሠረት፡ምግብነት፡ሲኾን፡
፫፡ግብር፡አለው። ሕይወተ፡ሕፃናት፡ነው፥ ያሳድጋቸዋል፤ ኃይል፡
ይሰጣቸዋል። ምንም፡፫፡ግብር፡ቢኖረው፡፩፡ሐሊብ፡እንጂ፥፫፡
አይባልም፤ እንደዚህ፡ኹሉ፡ሥላሴም፡በአካልና፡በአካል፡ግ
ብር፡፫፡ቢኾኑ፥ በባሕርይና፡በባሕርይ፡ግብር፡፩፡አምላክ፡እንጂ፡
ሦስት፡አይባሉም። ሐሊብ፡ለሕፃናት፡መዠመሪያ፡ምግብ፡

www.ethiopianorthodox.org

፩፱

የሬቶኛው፡ቃል፡ነው።

ጥያቄ፤ ጕንደ፡ወይን፡ከማግስኞ፡ፍጥረት፡ከዕፀዋት፡ኹሉ፡ተለይቶ፡
የሠላሴ፡አርኣያና፡አምሳል፡መኾኑ፥እንዴት፡ነው።

ምላሽ፤ ሉቱኤል፡ዕዝራ፡እምኵሉ፡ዐጣ፡ለምድር፡ወእምኵሉ፡ዕፀ
ዊሃ፡ኀረይከ፡ለከ፡አሐደ፡ዐጸደ፡ወይን፡ብሎ፡መመረጡን፡እን
ደ፡ተናገረ፤ እግዚር፡አስቀድሞ፡መሢሐቱና፡ምሳሌው፡ሊኾን፡
ስለ፡መረጠው፡ነው። ዐጸድ፡ያለውም፡ዛፉን፡እንጂ፤ ቦታውን፡
አይደለም።(ተረፈ)፤ ዐጸድ፡የሌለው፡ዱብር፥ጽሕም፡የሌለው፡
መምር፡እንዲሉ። ምሳሌነቱም፡እንዲህ፡ነው፤ ዳዊት፡ስለ፡
ቤተ፡እስራኤል፡ዐጸደ፡ወይን፡አፍለስከ፡እምግብጽ፤ ሰደድከ፡
አሕዛበ፡ወተከልከ፡ኪያሃ፡ያለውን፥ሰሎሞንና፡ኢሳይያስ፥
ዐጸደ፡ወይን፡ኮነ፡ለሰሎሞን፡በብዔላሞን። ዐጸደ፡ወይን፡ኮነ፡
ለፍቁር፡በብሔር፡ጕሉል፡ብለውታል። ጌታም፡በወንጌል፡በማ
ቴዎስና፡በዮሐንስ፥ብእሲ፡በዓለ፡ቤት፡ተከለ፡ዐጸደ፡ወይን፤
ወድኅረሰ፡ሬነወ፡ወልዶ። አነ፡ውእቱ፡ዐጸደ፡ወይን፡ዘጽድቅ፤
ወአቡየ፡ተካሊሁ፡ብሎ፡ባለቤትነትን፡ለአብ፡ሰጥቶ፡ተናግሯል።
ወይን፡ያንድነት፡ስም፡ነው። ጕንዱም፡ሐረጉም፡ቅጠሉም፡ፍሬ
ውም፡ወይን፡ይባላል፤ ጕንድ፡ግን፡ሳይለይ፡የልዩነት፡ስም፡ነው።
ሊቁም፡አባ፡ሕርያቆስ፥እንዲህ፡ከብሉይ፡ከሐዲስ፡አያይዞ፤
ይልቁንም፡የወልድን፡ጕንድነት፡ተመርኵዞ፥አብ፡ጕንደ፡ወይን፤
ወልድ፡ጕንደ፡ወይን፤ ወመንፈስ፡ቅዱስ፡ጕንደ፡ወይን፡ብሎ፡፫ነ
ታቸውን፤ አሐዱ፡ውእቱ፡ወይነ፡ትፍሥሕት፡ዘቦቱ፡ኅሠመ፡
ኵሉ፡ዓለም፡ብሎ፡፩ነታቸውን፡ተናገረ። ጕንድነታቸውም፡
ለፍጥረትና፡ለነቢያት፡ለሐዋርያት፡ነው፤ ስለ፡ምን፡ቢሉ፥መፍ
ጠር፡ማስገኘት፥ፍጥረቱን፡እንዲባት፡መርገም፡መባረክ፥መ
ርጦ፡መሾም፥መላክ፥በሰው፡ዐድሮ፡መስበክ፤ ይህ፡ኹሉ፡የባ
ሕርይ፡ፍሬያቸው፥ያንድነት፡ግብራቸው፡ነውና፤ ስለዚህ፡ጕ
ንድ፡ተባሉ። ምንተ፡እረግም፡ዘእግዚአብሔር፡ኢረገመ።

www.ethiopianorthodox.org

